የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት
ETHIOPIAN CIVIL SOCIETY ORGANIZATIONS COUNCIL

ቁጥር/Ref.No: ኢ.ሲ.ማ.ድ.ም/ሒ7 332/11
ቀን/Date ህዳር 27/2015 ዓ.ም

# መግለጫ

<u>የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በምዕራብ ኦሮሚያ ምሥራቅ ወለጋ በዜጎች ላይ እየደረሰ ያለው ሞት፣ መፈናቀል እና ሰቆቃ በእጅጉ እንደሚያሳስበው እየገለጸ መንግስት የዜጎችን ደህንነት የማረጋገጥ ሃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ ጥሪውን ያቀርባል</u>

ህዳር 27 ቀን 2015 ዓ.ም አዲስ አበባ፦ የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በሃገራችን የሚገኙ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን ለማስተባበርና ለመወከል በአዋጅ የተቋቋመ መሆኑ ይታወቃል። ምክር ቤቱ የሲቪል ማህበረሰብ ዘርፉ አገራዊ ፋይዳ ባላቸው ጉዳዮች በአግባቡ እንዲወከል እና የተቀናጀ ጥረት እንዲኖር የበኩሉን በመወጣት ላይ ይገኛል።

ምክር ቤቱ በተለያዩ ጊዜያት በሃገራችን ወቅታዊ የሰላምና ደህንነት ጉዳዮች ላይ በተከታታይ መግለጫዎች በማውጣት የዘርፉን ድምጽ ሲያሰማ ቆይቷል። በእነዚህ መግለጫዎች ላይ እንደተመለከተው የዜጎች ደህንነት እንዲረጋገጥ እና በግጭት ምክንያት ለተጎዱ ወገኖች የዕለት ደራሽ ሰብዓዊ ድጋፍ እንዲደርስ መንግስት እና ሁሉም ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን እንዲወጡ ጥሪ ሲያቀርብ ቆይቷል።

ሰሞኑን በምዕራብ ኦሮሚያ ምሥራቅ ወለጋ በቀጠለው ግጭት በዜጎች ላይ ጉዳት መድረሱን ከአካባቢው በሚወጡ መረጃዎች ምክር ቤቱ ተረድቷል። በዜጎች ላይ እየደረሰ ያለው ሞት፣ መፈናቀል እና ሰቆቃ ምክር ቤቱን በእጅጉ ያሳሰበው መሆኑን እየገለጸ፤

1ኛ) መንግስት በማንኛውም ሁኔታ የዜጎችን ሁለንተናዊ ደህንነት የመጠበቅ ሃለፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ፤

2ኛ) ብዥታን ለማስወገድ እና የተሳሳቱ መረጃዎችን ለማጥራቱ በጉዳዩ ላይ ወቅታዊ፤ተጨባጭ እና ትክክለኛ መረጃ ለህዝብ እንዲደርስ እንዲያደርግ፤

3ኛ) በአካባቢው ያለው ሁኔታ ተጣርቶ፤ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ፤

☎ (251) 11 853 2005/8/9
Email: ECSOC22@gmail.com
URL:www.ecsoc.net
@ethiopian.cso_council
@Eth_CSO_Council
@ethiopian_cso_council
Ethiopian Civil Society Organizations Council
Location: Left flank, 3rd floor, Hibr Building of Hibret Bank, Addis Ababa Ethiopia

4ኛ) አፋጣኝ ሰብዓዊ እርዳታ እና ድጋፍ ለተጎጂዎች እንዲቀርብ፣ እንዲሁም፣ ለጉዳዩ፣ ዘላቂ እና ሁለንተናዊ መፍትሄ እንዲፈለግ ጥሪውን ያቀርባል።

የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን ብሎም በየትኛውም የሀገራችን ማእዘናት የሚኖሩ የዜጎች ሁለንተናዊ ደህንነት እንዲረጋገጥ የጀመረውን የሰላም ግንባታ ስራዎች አጠናክሮ ለመቀጠል ያለውን ቁርጠኝነት እና ዝግጁነት በድጋሚ ለማረጋገጥ ይወዳል።

<u>*ስለ የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት*</u>

*የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 1113/2011 በአንቀጽ 85 መሰረት የተቋቋመ ምክር ቤት ሲሆን በኢፌዲሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ተመዝግበው ዕውቅና ያገኙትን የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን በመወከል በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲንቀሳቀስ በአዋጁ ኃላፊነት ተሰጥቶታል። በአሁኑ ወቅትም ከ4300 በላይ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የምክር ቤቱ አባላት ናቸው።*